# የቆንጆ መጽሄት "ቅብጥርጥሮሽ"

**እውነቱ ነጋ**

**09-18-14**

የዚህ ፅሑፍ መነሻ ቆንጆ መጽሔት በነሀሴ 2006 እትሟ የስደተኞቹ ጋዜጠኞች ምስጢር የሎሚ መጽሄት ባለቤት ኦነግ ነውን? በሚል ርዕስ ቴዎድሮስ ካሣ የመጽሄቱ ማኔጂንግ ኤዲተር መሆኑ ነው ዘለግ ያለ ፅሁፍ አስነብቧል፡፡ የፀሐፊው የመጀመሪያ ትኩረት በመጋቢት 1999 የወጣውን 'የኢሕአዴግ የፖሊሲ ወረቀት' ይለዋል ሰነድ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ትግልና አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሚል ርዕሰ ሥር ሚዲያና ደሞክራሲ በሚለው ላይ ትኩረት አድርጌ ነው የፃፍኩት የሚለው ቴዋድሮስ ካሣ ከፍሬው ገለባ የሆኑ መዘባዝቦችን አስፍሯል፡፡ ሰነዱ የምርጫ 97 ዝረራ የወለደው ነው፡፡ ሰነዱ ሚዲያ የዴሞክራሲ ሥርዓትን በመገንባት ረገድ ወሣኝ ድርሻ ካላቸው ተቋሞች አንዱ ነው ቢልም ዋና ግቡ ግን ሚዲያን እንዴት ማጥፋት እንደሚቻል የሚተነተን ነው ይላል ጸሐፊው፡፡

የሩዋንዳን እልቂት ፈጣሪ ሚዲያዎችን፣ የምዕራባውያን የሚዲያ ተቋማትን እንዲሁም በዐረቡ ዓለም ያሉትን አልአረቢያና አልጀዚራን በመጠቃቀስ ኪራይ ሰብሳቢ ሚዲያዎች የሚል ፅንስ ሀሳብ ለማዋል በሚረዳ መልኩ የኪራይ ስብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ በልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ በተሟላ መልኩ መተካት አለበት ብሎ ይደመድማል፣ ከዚህ በኋላ ኪራይ ሰብሳቢ ሚዲያ ሲባል አቤት ማለት ይኖርብናል ይላል ቴዎድሮስ ካሣ፡፡

ብስለትና ጭብጥ የጐደለውና በባዶ ሜዳ የሚጋልበው ይህ ጽሁፍ ከመነሻው እስከ ማካተቻው የፀሐፊውን የከፋ የአስተሳሰብ ድህነትና ባዶነት ያሳያል፡፡ጓደኞቼ ለሚላቸው  አገር ጥለው ለተሰደዱት እንደ ጓደኛ ፍቅሩንና ወዳጅነቱን መግለጽ ራሱን የቻለ አንድ ጉዳይ ሆኖ ጭርሱንም በማያውቀው ባልተረዳው ባህረ ሀሳብ ላይ ዘሎ ተደርግሞ በጭፍን ጥላቻ ተቃውሞን ማኅጐድጐድ ያው እንደተለመደውና እንደኖርንበት በተቃውሞ ስም ርካሽ ገበያና ገንዘብ ፍለጋ ከመዋተት የዘለለ አይደለም፡፡

በስሜት እየተነዱ በቁንፅል ሀሳብና በስማ በለው የሰማው ላልሰማው ያስማ በሚል እነ ቴዎድሮስ ካሣ በጡሩንባ ነፊነት በቅብብሎሽ እንደገደል ማሚቶ ሲያስተጋቡት የኖሩት መሠረተ ቢስ ወሬ፤ ስም ማጥፋትና የፈጠራ ዜና በየትኛውም መሥፈርት የሚዲያ ሥራ  አይደለም፤ ሊሆንም አይቻልም፡፡

ኃላፊነትና ተጠያቂነት ሚዛናዊነት ያለው የግል ሚዲያ በሕግ ተጠያቂ የሆኑትንም ሆነ እነ ቆንጆ መጽሔት የሚሰሩትን የወረደ ሥራ አይሰራም፡፡ የገንዘብ ትርፍ ማግኘትን ዓላማው አድርጎ በመነሳት በአገርና በሕዝብ ስም ኃላፊነት በጎደለው መልኩ አይነግድም፡፡ የሌሎችን ገበያ አይታ በማታውቀው ፖለቲካ ገብታ ለመንቦጫረቅ ተቃዋሚ ከተባልኩ ገበያ አገኛለሁ ከሚል የዋህ ሥሌት ድንገት ተነስታ የተዘፈቀችበት ነው፡፡ ሌሎቹም በሕግ ተጠያቂ የሆኑት መጀመሪያ የማህበራዊና የፍቅር መፅሄት ነበሩ፡፡

በብዙ ሺህዎች የሚቆጠር ብር የሚያስታቅፍ አክራሪና ፅንፈኛ የፖለቲካ ተቃዋሚ ኃይል ለገንዘብ አትቸገሩ የምንፈልገውን ሥራ ስሩ እንካችሁ ሲላቸው ተደንደርድረው መረቡ ውስጥ ገቡ፡፡ እጅግ ወገናዊ ኃላፊነት የጐደለው ለጥላቻ፣ ለሁከትና ለአመፅ  ሕዝብን የሚያነሳሳ፤ በግለሰቦች ላይ ያተኮረ የስም ማጥፋት ዘመቻ በቅጥረኛነት ሲያካሂዱ ከረሙ፡፡ ይህ ከጀርባ አይዞህ በሚለውና በከፍተኛ ፋይናንስ እየተረዱና እየታገዙ የአክራሪና ጽንፈኛ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፖርቲን አጀንዳ በግምባር ቀደምትነት በመጽሄቶችና ጋዜጣ  ሲያራምዱ የቆዩት ከጋዜጠኝነት ሥነ ምግባርና መርህ በፍፁም ተፃራሪነት የቆሙ ለመሆናቸው ሥራቸው ምስክር ነው፡፡

በተለያዩ አገራት የሚዲያ ነጻነት ሕጎች አሉ፡፡ የሚዲያ ነፃነት ስላለ ብቻ ጋዜጠኝነት ወይንም ጋዜጠኞች ከሕግና ከሥርዓት ውጪ ለራሳቸው የጥቅም ፍላጐት (ገንዘብ) ማግኚያ ወይንም የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማስፈፀሚያነት ሲሉ ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር እንዳሻቸው እየደፈጠጡና እየጨፈለቁ የግለሰብን፣ የተቋማትንም መብትና ክብር እየጣሱ እንዲሰሩ የሚፈቅድ ሕግ የትም የለም፡፡ በአገሪቱ የግሉ ፕሬስ አጭር እድሜ ያለው ሲሆን ገና ዳዴ በማለት ላይ የሚገኝ ነው፡፡

መብትና ነፃነት እስከምን ድረስ ይሄዳል?፣ ገደቡስ ምንድነው?፣ የማይታለፉት አጥሮችስ የትኞቹ ናቸው? የሚለውን ቁልፍ ጥያቄ ያላወቀ ሰው በጋዜጠኘነት ስምና ሥራ ተሰማርቶ እንደ ቴዎድሮስ ካሣ ሙያውን እሱና መሰሎቹ ለጥቅም ፍለጋ ሲሉ ከሚያራክሱት ይልቅ በአቅማቸው ሰርተው መኖር የሚችሉበትን ቢያማትሩ የተሻለ ነበር፡፡

በኢትዮጵያ የግል ጋዜጠኝነት መጀመሩ መልካም ቢሆንም ገና ተገቢ ሙያዊ፣ አገራዊና ሕዝባዊ ኃላፊነትን በብቃት ለመወጣት የሚችልበት ደረጃ ላይ አልደረሰም፡፡ይህ በሂደትና በእድገት ሊደረስበት የሚችል እንደሆነ ቢታመንም አሁን ባለበት ደረጃ በጣም ከጥቂቶች በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቋንቋዎች ከሚታተሙ ጋዜጦች በስተቀር አብዛኛዎቹ ብስለትና ብቃት፣ ሙያዊ ክህሎትና ሚዛናዊነት የሌላቸው ራሳቸውን ሆነው ለማደግ የሚሰሩ ሳይሆኑ በሌሎች ልሣንነት የተጠለፉና የተጠመዱ ናቸው፡፡ ከተራ ስም ማጥፋት፣ ከመንደር አሉባልታና ወሬ፣ ከጥላቻ ማስተላለፊያ መሣሪያነት ያልወጡና ያልተላቀቁ ናቸው፡፡

እንደ መጽሄት ወይንም ጋዜጣ ወይንም ሚዲያ ያለበትን የማስተማር፣ የማሳወቅ፣ የማዝናናት፣ ሚዛናዊና ግልጽነት፣ ተጠያቂነትን የሚያሟሉ አይደሉም፡፡ ስህተት ነው አርሙ አስተካክሉ ሲባሉም ፍፁም አዋቂዎችን ነን በሚል የሚታበዩ፣ ራሳቸውንም በጊዜና በሂደት ለማረም ጥረት የማያደርጉ፣ ተነሳሽነቱም የሌላቸው ናቸው፡፡ በሙያው እየበቁ ለመሄድ ሰፊው እድል በእጃቸው ያለና የነበረ ቢሆንም ዜናዎችና መጣጥፎችን ስሜታዊና ኮርኳሪ ናቸው ብለው ከሚያምኑባቸው ግነቶች ጋር የሚሰሩ ፍፁም ኃላፊነት በጎደለው መልኩ ገንዘብና ገንዘብ ማግኘትን ብቻ ዓላማ ያደረጉ ናቸው፡፡

ቴዎድሮስ ካሣ የስደተኞቹ ጋዜጠኞች ምስጢር በሚለው ፅሁፍ ስለግዛው ታዬ ኦነግ ተብሎ መታሰር፣ በግድ አስገድደው ኦነግ ነኝ እንዲል አድርገውት ከባሌ ከተለቀቀ በኋላ መታወቂያውን ይዞ ሞጆ ከተማ እንደገባ ነግሮናል፡፡ ሞጆ ከተማ መግባቱን እንቀበል ግን ግን ቴዎድሮስ ካሣ አስገድደው ኦነግ ነኝ እንዲል አደረጉት ሲል ምን ለማለት ፈልጐ ነው? ይህ ነው እንግዲህ የለመዱትና ሲነግዱበት የኖሩት አሳፋሪ ሥራ፡፡የኢትዮጵያ ፖሊስ ወይንም የፀጥታ ክፍል እየገረፈና እየደበደበ ሰዎችን

በግድ ያልሰሩትን ወንጀል እንዲያምኑ ያደርጋል የሚለውን የተሳሳተ መልዕክት ቴዎድሮስ ካሣ ለአንባቢያን መንገሩ ነው፡፡

ግለሰቡ በፖሊሲ ይኼ ደረሰበት ቢባል እንኳን ለፍርድ ቤት ሲቀርብ የደረሰበትን በደል ገልጾ ማስተባበል እንደሚቻል የታወቀ ሆኖ ሳለ ስለዚህ ጉዳይ ፀሐፊ ነኝ የሚለው ግለሰብ አያነሳም፡፡ ስለዚህም የተለመደ ስም ማጥፋትና ውንጀላን ቴዎድሮስ ካሣ ራሱ እያካሄደ ነው፡፡

የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሚለው ሰነድ ላይ ስለሚዲያ በንዑስ ክፍል የተገለፀውን ሀሳብ ለማብጠልጠል የከጀለው ቴዎድሮስ ካሣ አብዮታዊ ዴሞክራሲና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምን እንደሆነ፣የሚዲያ ባሕርያትና ዓላማና ምን እንደሆነ ምንም ዓይነት ተጨባጭ እውቀትና ግንዛቤ እንደሌለው ፅሁፎቹ ያስረዳሉ፡፡በጭፍንና በጥላቻ ለመቃወምና ለመተቸት የተነሳ ደፋር መሆኑን ያነበበ ይረዳዋል፡፡

የኢትዮጵያ የግል ፕሬሶች መሠረታዊ ችግርም ይኸው ነው፡፡ ቁንፅል ሀሳብን ይዞ እንደገደል ማሚቶ ከማስተጋባት ያለፈ እንደ ጋዜጠኛ ጥልቀት ያለው ንባብ የሚያደርጉ፣ የሚፈትሹና የሚጠይቁ አይደሉም፡፡ በከፋ ሁኔታ የተገኘችውን፣ የሰሙትን ወይንም ያዩትን ፅፎ ለዕለታዊ ገቢ ማስገኛ ከመሮጥ ውጭ ሰፊ ግንዛቤ ለመጨበጥ በማል፣ በፍተሻና በምርምር ፅሁፎችን ለማስነበብ የሚተጉ አይደሉም - ትናንትም ዛሬም፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሲባል ለቴዎድሮስ ካሣና ለተቃዋሚው የሚታያቸው ኢሕአዴግ ነው፡፡ የኒዮ ሊበራል ፖለቲካል ኢኮኖሚ አቀንቃኞች፣ የአገርም የዓለምም ሀብት በዓለም አቀፍ ከበርቴዎች ሥር ሙሉ በሙሉ መያዝ አለበት የሚሉት በሙሉ አብዮታዊ ዴሞክራሲን አምርረው ይጠሉታል፡፡ ምክንያቱም በሕዝብ የበላይነትና የሐብት ባለቤትነት የሚያምን፤ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ከድህነትና ኋላ ቀርነት የሚያወጡ ሕዝብንም ተጠቃሚ የሚያደርጉ መንገዶችን ስለሚከተል ነው፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ትልቅ ፅንሰ ሐሳብ ነው፤ ሩሲያና ቻይናን ኮሪያን ወዘተ… ከድህነትና ከኋላ ቀርነት አረንቋ አውጥቶ ወደ ታላቅ የኢኮኖሚና የፖለቲካ

ኃያልነት የለወጠ፤ ያበቃ በራስ ሕዝብ አቅም ጉልበት ሐብት የፈጠራ ችሎታና የሥራ ብቃት ትጋት ሕዝቡን ተጠቃሚ ያደረገ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መንገድ ነው፡፡

በቻይና አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ተብሎ ሲጠራ ምንም ዓይነት ዘመናዊ ፋብሪካና ከባድ ኢንዱስትሪ ያልነበራትን፤ በኋላ ቀርና ጥንታዊ ግብርና ላይ ብቻ ትኖር የነበረችን ድሀ አገር የዘመናዊ ፋብሪካ፣ ተቋማት፣ ኢኮኖሚ ባለቤት በማድረግ ግብርናውን ወደ ሜካናይዝድ እርሻ በመለወጥ፤ መንገድ፣ ትምህር ቤት፣ ጤና አገልግሎት ወዘተ... በማስፋፋት ቴክኖሎጂ በማሳደግ ወደ ቀጣዩ የጐለበተ አገራዊ ኢኮኖሚ ያሸጋገራት ድልድይ ነው - አብዮታዊ ዴሞክራሲ፡፡

ቻይና ዛሬ ያለችበትን የዓለም ኃያል ኢኮኖሚነት ደረጃ የደረሰችው በዚህ መንገድ ተጉዛ ቀጣዩን ታላቅ ምዕራፍ በመሸጋገር ነው፡፡ ዛሪስት ሩሲያም ከ1917ቱ የታላቁ ጥቅምት አብዮት ድል በኋላ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከኋላቀርና ባላባታዊ ሥርዓት ለማውጣት በዚሁ የሽግግር መንገድ ተጉዛና መሠረት ጥላ ነው የታላላቅና ከባድ ኢንዱስትሪና ፋብሪካዎች ባለቤት በመሆን በሁሉም መስክ ከፍተኛ የኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ ስኬትና ድል ያስመዘገበችው፡፡

በዓለም ወሣኝና ተደማጭ የፖለቲካ ኃይል ለመሆን ያስቻላቸውን ስኬት የተጐናፀፉበት ነው አብዮታዊ ዴሞክራሲ፡፡ ምኑንም የማያውቀው ጨዋው ቴዎድሮስ ካሣ የሚሉትን እየሰማ በጭፍን አስተሳሰቡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እያለ ሊያላግጥ ይከጅላል፡፡ አለማወቅንም አውቆ መሰብሰብ ወይንም ለማወቅ መጣጣር ብልህነት ነው፡፡ ዘሎ በጭቃ ረጋጭነት የማያውቁትን ነገር በደርሶ አዋቂ ነኝ ባይነት ማቡካት ደግሞ ነውረኛ ተግባር ነው፡፡

ያፋጠጠውን እውነት እንነጋገር ከተባለ በግል ጋዜጠኝነት ስም መጽሔትና ጋዜጣ አሣታሚዎች በአገሪቱ የንግድ ሕግ የተመዘገቡ ነጋዴዎች ናቸው፡፡ ስለዚህም ጋዜጣና መጽሐታቸውን እንደሸቀጥ በመሸጥ የገንዘብ ትርፍ ለማግኘት የማትሉትና የማትጽፉት ነገር እንደሌለ ይታወቃል፡፡ እርስ በእርስም የንግድ ፉክክር ታደርጋላችሁ፡፡ የበለጠ ጥቅም አግኝቶ ለመክበር ያደረባችሁ ስግብግብ ፍላጐታችሁ

ደግሞ ወሰንና ድንበር እንድታልፉ በማድረግ ከጀርባ ያሉትን የገንዘብ ምንጮቻችሁን ለማስደሰት የማትፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡

ይኼ የጥቅም ጥገኝነትና ተገዢነት ነው ከሙያው ውጭ እየሄዳችሁ ከህግና ሥርዓት ጋር እያላተማችሁ ያለው - አፈቀላጤና ልሣን በመሆን፡፡ እናንተ ደግሞ ለአገር ለሕዝብ ስንል ነው የምንሰራው ብላችሁም ትዛበታላችሁ፡፡ ነገር ግን የአገርና የሕዝብን አብሮነት ፍቅር፣ መቻቻል፣ መከባበር፣ መደማመጥ የሚንድና የሚያፈርስ፤ እርስ በእርስ የሚያጋጭ፤ በጠላትነት እንዲተያይ የሚያደርግ፤ ወደመጠፋፋት የሚያመራ የጥላቻ መርዝ ትነዛላችሁ፡፡

በዚህም የአገር ቀውስና ሠላም ማጣት ደንታችን፣ ነግደን እናተርፋለን እንከብራለን፤ የፈለገው ቢሆን እኛ ምን አገባን፤ ጉዳያችን ከገንዘቡ እንጂ ከሌላ አይደለም በሚል ስግብግብና አውሬያዊ አስተሳሰብ የፕሬስ ነፃነትንና የሚዲያ ነፃነትን ሽፋን በመጠቀም እየሰራችሁ በህግ ተጠያቂ ስትሆኑ የፕሬስ ነፃነት የለም ትላላችሁ፡፡ እናንተው እውቀት አልባ በሆነው አስተዋይነት በጎደለው ያልተገራ ብዕራችሁ የተጋጋመ ንዳድ ለማስነሳት ወናፍ ስትነፉ ከርማችሁ በፈጠራችሁት ችግር ህግ ሲጠይቃችሁ እሪታችሁ ጣሪያ ቀድጄ ልውጣ ይላል፡፡ ስትሰሩ የነበራችሁትም እየሰራችሁ ያላችሁትም ኃላፊነት በጎደለው ሁኔታ ለራሳችሁ ጥቅምና ትርፍ ለማግኘት እንጂ ስለአገርና ስለሕዝብ ሠላም እድገት ልማት እንዳልሆነ ውስጣችሁ ጠንቀቆ ያውቃል፡፡

ቴዎድሮስ ካሣ ስለ ኪራይ ሰብሳቢነትም ያነሳል፡፡ አሁንም በቴዎድሮስ ካሣና ከእውቀት በተፋቱ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች አሳፋሪ አባባል ኪራይ ሰብሳቢነትን ኢሕአዴግ የፈጠረው ቃል ወይንም ኢሕአዴጋዊ አድርገው ሊሳለቁ፤ ሊያሾፉ ይከጅላቸዋል፡፡ ምን ያህል አላዋቂዎች መሆናቸውን ቢከፍቷቸው ባዶ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ማፈሪያዎችና አሳፋሪዎች ናችሁ፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነት /rent seeker) በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው ታላላቅ ኢኮኖሚስቶች የምጣኔ ሀብት ሊቃውንት የሚጠቀሙበት የኢኮኖሚ ጽንስ ሀሳብ ነው፡፡ አዳም ስሚዝ ዘ ዌልዝ ኦፍ ኔሽንስ በተባለው ታላቅ መጽሀፉ ከ150 ዓመታት በፊት ተጠቅሞበታል፡፡ በዚህ ኢኮኖሚስት ምዕራቡ ዓለም ያመልክበታል፡፡

ከአዳም ስሚዝ በኋላ እነካርል ማርክስና ሌሎችም ተጠቅመውበታል፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነት ቃሉ /ሬንት ሲከር/ ያን ያህል ጥንታዊ ነው፡፡ ጥገኛ፣ ተውሣክ፣ ፓራሣይት ማለት ነው፡፡ሰርቶ ለፍቶ ደክሞ በሚያገኘው ሳይሆን ሌሎች የደከሙበትን የሚነጥቅ፤ ተመሳጥሮ የሚዘርፍና የሚበላ፤ ከባለሥልጣኑ ተጠግቶ በሕገ ወጥ መንገድ በወንጀል ሐብት ገንዘብ ለማግኘት፣ ያልደከመበትን ለመዝረፍ የሚሰራ ማለት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ አለመታደል ሆኖ በሁሉም ትላልቅ መስክ የግሉንም ሚዲያ ጨምሮ እልቆ መሣፍርት ኪራይ ሰብሳቢዎች ያሉባት የነገሱባት አሳዛኝ አገር ናት፡፡

በላቡ ሰርቶ ከሚኖረው ነጥቆ አምታቶ በምላሱ ነግዶ አጭበርብሮ ሐብታምና ከሙሰኛ ባለሥልጣን ተጠግቶ የመንግሥትንና የሕዝብን ሐብትና ንብረት በሥውር በጥገኛ ፓራሣይትነት እየመዘበረ የሚኖረው፤ የሙስና አቀባባዩና ኪራይ ሰብሳቢው ባልለፋበት ሐብት የከበረው ብዙ ነው፤ ይህንን ሂደትና ጊዜ ያወጣዋል፡፡

ቴዎድሮስ ካሣ መቼም ከእውቀት የተፋታ ደፋር ሰው ነውና መጽሄት ስላለው፤ ፅፎ ማሣተም ስለቻለ ራሱን ከጣሪያ በላይ ቆልሎታል፡፡ ሰዎች ምን ይሉኛል የሚል ትንሽ ይሉኝታም የሌለው ጨዋ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ኪራይ ሰብሳቢ ሚዲያ ሲባል አቤት ማለት ይኖርብናል ይላል፡፡ በሌላ አንቀጽ ደግሞ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚዲያ አንቀጽ ላይ የተቀመጠው የውጊያ ግንባር የሚዲያ አውታሮች ገቢና ወጪያቸውን በትክክል እንዲያስመዘግቡና በየጊዜውም ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግበት ማድረግ ወሣኝ ጉዳይ ነው መባሉን ይገልጻል፡፡

ይህም የሚረዳው በውጪ ኃይሎችና በፀረ ሠላም ድርጅቶች የግል ሚዲያው ፋይናንስ እንዳይደረግ በጥብቅ መከላከልና መቆጣጠር በጣም አስፈላጊ ይሆናል ተብሎ መገለጹን ቴዎድሮስ ካሣ በፍርሀት ተውጦ ይነግረናል፡፡ ግለሰቡ ምንም ዓይነት ሰፊ ግንዛቤና እውቀት ስለአገርም ስለሚዲያም የሌለው ቁንፅል ሀሳቦችን እየቀነጨበ ስለማያውቀው ጉዳይ ሁሉ በድፍረት የሚዘባርቅ ኅበዝ መሆኑን ጽሁፉ በገሀድ ይነገርናል፡፡ የአውሮፓ አገራትና አሜሪካን እንግሊዝም ብሔራዊ

ጥቅማቸውን ለማስከበር፣ የሕዝባቸውን ሠላም ለማስጠበቅ የሚከተሉት መንገድ ይኸው ነው፡፡

የውጭ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ኃይል ወይንም አክራሪ ኃይማኖታዊ አሸባሪ ድርጅት፣ የዓለም አቀፍ የማፊያ ቡድን ውንም ሌሎች የአገራትን ፈርጀ ብዙ ምስጢር ለመሰለል በአገራቸው የሚገኙ ሚዲያዎችን በገንዘብ እየረዱ የራሳቸውን ፍላጐትና ዓላማ እንዲያራምዱ የየትኛውም አገር መንግሥት አይፈቅድም፡፡ የፀረ ሠላምና አሸባሪ ኃይሎች ገንዘብ በየትኛውም አገር የግል ሚዲያ ተቋማት ውስጥ ገብቶ እንዲሰራ የሚፈቅድ ሕግ በዓለም ላይ የለም፡፡

እንዲያውም ከዚሁ የአክራሪዎች ጉዳይ ጋር በተየያዘ በርካታ የሚዲያ ተቋማት ድረ ገፆች (ሶሻል ሚዲያ) የቴሌቪዥንና ራዲዮ ጣቢያዎች፤ የግል መጽሄትና ጋዜጦች በአውሮፖ በአሜሪካ በዐረቡ ዓለም ታግደዋል፤ ተዘግተዋል፡፡ የባንክ አካውንታቸውም ተዘግቷል፡፡ ይህ አሠራር በንጉሱ ጊዜም በደርግም ሆነ ዛሬ ቀጥሏል፡፡ ዛሬን የተለየ የሚያደርገው በኢሕአዴግ ዘመን ከሚዲያ ነጻነት አንፃር የግል ሚዲያ መከፈቱና መኖሩ ነው፡፡

ይህም ለተባሉት ጉዳዮች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ስለሆነ ብሄራዊ ጥቅምን፣ አገራዊ ደህንነትን፣ ሠላምን ለሚፈታተኑ ኃይሎች መሣሪያ እንዳይሆን በጥብቅ መከታተል ሁሉም መንግሥታት የሚያደርጉት መደበኛ ሥራ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ አገራዊ ህልውና በተቃራኒ ለቆሙ ኃይሎችና አገራት ወይንም በአክራሪና አሸባሪ ኃይሎች አልሸባብ አልቃይዳና ሌሎችም በሥውር የሚታገዝ በግል ሚዲያ ስም የሚንቀሳቀስ የግል ፕሬስ በኢትዮጵያ ቢኖር የፕሬስ ነፃነት ስለሆነ መብቱ ነው የሚል ጅላጅል ሀሳብ ሊያነሳ ነው የሚከጅለው ቴዎድሮስ ካሣ፡፡

መቼም የአስተሳሰብ ጠባብነትን የመሰለ ክፉ በሽታ የለምና ይህ የተደረገው ተቃዋሚውን መላወሻ ለማሳጣት ነው የሚል ተልካሻ ምክንያት ያቀርባሉ፡፡ ከሁሉ በላይ ግዙፍ ስለሆነችው አገር ስለብሔራዊ ጥቅሟ፣ ደህንነቷ፣ ሠላሟ፣ ስለሐብቷና ስለሕዝቧ ለጥቃት ሳይጋለጥ መጠበቅ አያሳስባቸውም፡፡ እንዲህ ዓይነትም ዜጎች አሉ፡፡

ይኸው ጉዳይ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚዲያ ንዑስ ክፍል ላይ በግልፅ ሰፈረ እንጂ ከኢሕአዴግ በፊት የነበሩትም ሆነ ከኢሕአደግ በኋላ አገር ለመምራት ወደ ሥልጣን የሚመጣ ቢኖር ይህንን ተግባራዊ ማድረግ የግዴታም ግዴታው ነው፡፡ የግሉ ሚዲያ ለእነዚህ ኃይሎች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ለመሆኑ የተለያዩ የዓለም አገራት ተጨባጭ ማስረጃዎችን በምስክርነት መጥቀስ ይቻላል፣ የቴዎድሮስ ካሣ እይታና ግንዛቤ በጣም ጠባብና ካለበት ቢሮ የዘለለ ባለመሆኑ የሚጠበቅ ነገር የለም፡፡ እንዲያው ፊትን አሳምሮ እየለጠፉ ማኔጂንግ ዳይሬክተር እያሉ ጠያቂ የሌለበትን ትልቅ ስም ለራስ እየሰጡ በባዶ ሜዳ ከመኮፈስና ከመዘባረቅ ይልቅ ቁሶቹ ሲነቅፉ እንደሚሉት ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም፣ ማወቅ ይቅደም፣ ማንበብ ይቅደም ማለቱ መማር ከቻለ ለዚህ አላዋቂ ጉበዝ ይጠቅመዋል፡፡

ሚዲያ ምን ያህል የገዘፈ አቅም እንዳለው ቴዎድሮስ ካሣ ጋዜጠኛ ነኝ ብሎ ከመኩራራት በጥራዝ ነጠቅነት ከመታበይ ውጪ የሚያውቀው ነገር የለውም፡፡ ቢያነብ አብዮታዋ ዴሞክራሲ ስለሚዲያ ጻፈው በሚለው ላይ ያቀረበውን እውነት የሚክድ ማነው? በሩዋንዳ የደረሰው የዘር እልቂት አንድ ሚሊዮን ሕዝብ እንዲጠፋ ምክንያት የሆነው አንድ ዘረኛ ጋዜጠኛ በራዲዮ ባስተላለፈው መልዕክት ነው፡፡

የምዕራባውያን ግዙፍ የሚዲያ ተቋማት የኒዩ ሊበራሉ ዓለም አቀፍ ከበርቴ ቀኝ ክንድ በመሆን የኢኮኖሚ ጥቅምና ፍላጐታቸውን ለማስከበር ሲሉ በበርካታ አገራት ላይ በከፈቱት የሥነ ልቦና ጦርነት የእርሰ በእርስ ግጭት እንዲነሳ ቤንዚን በማርከፍከፍ አገራቱን በትርምስ እንዲፈራርሱ አላደረጉም? አልጀዚራ ቲቪ በዐረቡ ዓለም አብዮት ከገለልተኛ የሚዲያ ተቋምነት ይልቅ የጦር መሪና አዝማች ጄኔራል በመሆን እነ ሊቢያን፣ ግብፅን፣ ሶሪያን በእልቂትና በደም መፋሰስ እንዲታጠቡ፣ ሕዝቡ በተለያዩ አንጃዎች ተከፋፍሎ እንዲተላለቅ፣ መንግሥት እንዲፈርስ፣ ሕግና ሥርዓት እንዲጠፋ፣ ሥርዓተ አልበኝነት እንዲሰፍን፣ አሸባሪዎችና አክራሪዎች ይበልጥ ታጥቀውና ተደራጅተው ጥፋት እንዲያደርሱ አላደረጉም?

ዛሬ ዓለምን በሥጋት እየናጣት ያለው በኢራቅና ሶሪያ መሐል የተመሠረተው የእስላሚክ ካሊፋይት መንግሥት (አይሲሴስ)፣ የናይጄሪያውን ቦኮ ሐራም፣ የማሊውን

አንጣር ዲና፣ እነ አልቃይዳን፣ እነ አልሻባብን እያራገበ እዚህ ያደረሳቸው ሚዲያው መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡

ቴዎድሮስ ካሣ ቆንጆ መፅሔትን ከጀመረ ጥቂት ዓመት ቢሆንም ትናንት ምንም እንዳልነበረው በቅርብ የሚያወቁት ይናገራሉ፡፡ ዛሬ የመኪና ባለቤት፣ የሌላ ንግድ ባለቤት፣ የብዙ ሺህ ብር ቢሮ በኪራይ ከፍሎ፣ በርካታ ሠራተኞች ቀጥሮ ደመወዝ ከፍሎ ይኖራል፡፡ ከኢትዮጵያ ራዲዮ በሥነ ምግባር ጉድለት ከተባረረ በኋላ በአንድ ጊዜ ይህ ግለሰብ ይህን ትልቅ የገንዘብ አቅም ከየትና እንዴት አገኘው? ከቤተሰቦቹ ወረሰው እንዳይባል እሱም እንደማይሆን ያውቃል፡፡ ከሰማየ ሰማያት ወረደለት እንዳይባልም ችግር ነው፡፡ በአንዴ የተስፈነጠረው ከየት በተገኘ ገንዘብ ነው ተብሎ ቢጠየቅ ማጣፊያው ያጥርበታል፡፡ 'ዓሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል…' ዓይነት ነው የሚሆንበት፡፡

ዛሬ ለማግኘትም ለመታወቅም የበቃው በአገሪቱ የፕሬስ ነፃነት ሕግ በመኖሩና ለመሥራት በመቻሉ ነው እንበል፡፡ በአግባቡና በህጉ እስከሰሩ ድረስ አትስሩ ያላቸው የሚላቸው ሕግ መቼም አይኖርም፡፡ የሆነ ያልሆነውን እየፃፍኩ ለስደት የሚያበቃኝን ማስረጃ እይዛለሁ፣ እናም ነገ አሜሪካን እገባለሁ ብሎ ከሆነም ወደውንጀላ የተሰማራው ምርጫው የራሱ ነው፡፡ በሠላም ሰርቶ በአገሩ መኖሩ የተመረጠ ነው፡፡

ለስደት የሚመች አሜሪካን አገር ፍርድ ቤት የሚቀርብ እያሉ መፃፍ የተበላ እቁብ ነው፡፡ እንደሚባለው ስለሆነም አያስገርምም፡፡ የዓይጥ ምስክር ድምቢጥ ሆኖ እንጂ የተሰደዱት ጋዜጠኞች ሥደት ናፋቂዎችና በልማንነት ይሰሩ የነበሩ ለመሆናቸው አቶ ቴዎድሮስ አያውቅም ለማለት ይከብዳል፡፡ እኔም እከተላችኋለሁ አሜሪካን እንገናኝ ማለቱን ግን መጠርጠር ይቻላል፡፡